# የቆቦ አመጽ እንደቀጠለ ነው | ከመቀሌ የተነሳ ልዩ የአግአዚ ጦር ማምሻውን ቆቦ ዳር መድረሱ ታዉቋል

January 25, 2018

ቢቢኤን ቆቦ ድረስ በመደወል ነዋሪዎቹን አነጋግሯል።የከተማው አስተዳደር ግልጋሎት እየሰጠ አይደለም።ፍርድ ቤት፣ማዘጋጃ ቤት፣የቀብሌ ጽ/ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያዎች የንግድ ድርጅቶችና ቤቶች ተቃጥለዋል።
የቆቦ ህዝብ በደንብ የታጠቀ መሆኑን የገለጹት ያካባቢው ነዋሪዎች ሌሊቱን በሙሉ ሲተኩስ ማደሩን ተናግረዋል።ከትግራይ ክልል አስር መኪናዎች ተጭነው የመጡ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከተማው ዉስጥ ሳይገቡ ዳር ላይ እየተጠባበቀ መሆኑ ታዉቋል።

ያካባቢውን ነዋሪ “አርፋቹ ተቀመጡ እኛ ተዘጋጅተናል” በማለት ያስፈራራ የነበረ አንድ የከተማው ባለጸጋ ንብረቱ ሙሉ በሙሉ መውደሙ ታዉቋል።ነጋዴው በቀን ስራ የሚተዳደሩብ ቆቦ ነዋሪዎች የቀንድ ከብቶች የሚመገቡት ፉርሽካ የናንተ ምግብ ነው ማለቱ በቆቦ፡ህዝብ ህልዉና ላይ የመጣ በመሆኑ ህዝቡ ታጋሽ መሆን አልቻለም ሲሉ የቆቦ ነዋሪዎች ለቢቢኤን አሳውቀዋል።

የቆቦ ህዝብ ነጻነትና ሰላም የጠማው መሆኑን ማወቅ የሚቻለው የህወሃት ሰላዮችና ደጋፊዎች ንብረትን ሲያቃጥል ጥሬ ብርን ሳይቀር አቃጠለ እንጂ ወደ ኪሱ አላስገባም ብለዋል የቆቦ ነዋሪዎች። ትላንት በጀመረው ህዝባዊ አመጽ ሁለት ሰዎች ሲሞቱ ሁለት ሌሎች ደግሞ ቆስለዋል። አንድ የፌደራል ፖሊስ መሞቱ ተረጋግጧል።

ሒሊኮፕተር ጥቃት አደረሰ የሚለውን ዜና የቆቦ ነዋሪዎች ምንም እንደማያውቁ ገልጸዉልናል።

ከነዋሪዎቹ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ በማታው ስርጭታችን ይጠብቁ።

#አሁን የደረሰን መረጃ:

በራያ ቆቦ ትናት ቀንና አዳሩን በቀጠለው ተቃውሞ በርካታ የመንግስት ተቋማት ጋይተዋል። ከቆቦ ሮቢት የተነሱ ወጣቶች ቆቦ ለመግባት ትንሽ ሲቀራቸው ሆርማት ተብሎ እሚጠራው ወንዝ አካባቢ ቆሞ ከሚጠብቃቸው ታጣቂ ሀይል ጋር ሲፋለሙ ቢውሉም ወደ ቆቦ ማለፍ እንዳልቻሉ ታውቋል።

ከመቀሌ የተነሳ ልዩ የአግአዚ ጦር ማምሻውን ቆቦ ዳር መድረሱ ታዉቋል። እንደወልደያ ሁሉ ማንም የክልሉ ባለስልጣን ወደ ቆቦ አልመጣም። አዳሩን ምን እንደሚፈጠር ስለማይታወቅ የቆቦን ህዝብ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በጸሎት (በዱአ) ያስታውሰው።